# ለዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት

# ዕጩዎች ማቅረቢያ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ

**ታህሣስ 2015 ዓ.ም**

# ማውጫ


መግቢያ ........ 2

1. አጭር ርዕስ ........ 2
2. ትርጉም ........ 2
3. የአስመራጭ ኮሚቴ አመሠራረት ........ 3
4. የአስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛና የአባላቱ ስብጥር ........ 3
5. የዳሬክተሮች ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት ........ 4
6. የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት ........ 4
7. የአስመራጭ  ኮሚቴው ደንብና ሥርዓት ........ 4
8. ለዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን የማቅረብ ሂደት ........ 6
9. የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ ሂደት ........ 9
10. የምርጫ አፈፃፀም ሥርዓት ........ 10
11. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የማይሆንበት ሁኔታ ........ 10
12. መመሪያ ስለማዘጋጀት ........ 11
13. ሌሎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሕጎች ........ 11
14. ይህ መመሪያ በጥብቅ ስለመፈፀሙ ........ 11
15. መመሪያውን ስለማሻሻል ........ 11
16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 11

## መግቢያ

የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመልካም አስተዳደር አንዱ መርህ የሆነውን የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ግልፅነት በተሞላበት መንገድ እንዲካሄድ ማድረግ ይጠቅበታል። ታማኝነት፣ የአመራር ችሎታና ብቃት ያላቸው ግለሰቦች የቦርድ ኃላፊነት ሲይዙ ለመልካም አስተዳደር መርህ መተግበር ያለው አጋዥነት የላቀ ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ ዕጩዎችን በመመልመል፣ አስፈላጊውን መረጃ በማጠናቀርና በማጣራት ለጠቅላላ ጉባኤው የሚያቀርብና ምርጫውንም የሚያስፈጽም ኮሚቴ ማቋቋም ወሳኝ ጉዳይ ነው።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰውን ተግባር ለማስፈፀም ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመልካም አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/71/2019 አንቀፅ 6.1.7 ለባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሁም በአንቀፅ 10.4.1 ለዳይሬክተሮች ቦርድ በሰጠው ሥልጣን መሠረት በዳይሬክተሮች ቦርድ ተዘጋጅቶ በባንኩ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ፀድቋል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የፀሐይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች ማቅረቢያ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

**"ባንክ/ባንኩ"** ማለት የፀሐይ ባንክ አክሲዮን ማህበር ነው።

**"ቦርድ"** ማለት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።

**"ዋና ሥራ አስፈፃሚ"** ማለት የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራን በዋናነትና በበላይነት የሚመራ ሰው ማለት ነው።

**"ዳይሬክተር"** ማለት የባንኩ የቦርድ አባል ነው።

**"ሠራተኛ"** ማለት የባንኩን ሥራ እንዲያከናውን በባንኩ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ሠራተኛ ማለት ነው።

**"ጠቅላላ ጉባዔ"** ማለት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ነው።

**“ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን”** ማለት ከተፈረመው የባንኩ ጠቅላላ ካፒታል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁለት በመቶ (2%) ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ ያለው ነው።

**“ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን”** ማለት ከተፈረመው የባንኩ ጠቅላላ ካፒታል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሁለት በመቶ (2%) ያነሰ ድርሻ ያለው ነው።

**“አስመራጭ ኮሚቴ”** ማለት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን ለማቅረብና ምርጫ ለማስፈፀም በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ኮሚቴ ነው።

**"ድምጽ"** ለዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን በሚቀርብበትና ምርጫ በሚደረግበት ወቅት ለድምጽ አሰጣጥ ታሳቢ የሚደረገው የተፈረመ አክሲዮን ነው።

## 3. የአስመራጭ ኮሚቴ አመሠራረት

3.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሥራ ላይ ያለው ቦርድ የአገልግሎት ጊዜ ሊያበቃ አንድ ዓመት ሲቀረው የአስመራጭ ኮሚቴውን ይመርጣል።

3.2 የአስመራጭ ኮሚቴው አባሎች ቁጥር አምስት (5) ይሆናል።

3.3 ጠቅላላ ጉባዔው ለዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት የዕጩዎች ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ ያፀድቃል።

3.4 ጠቅላላ ጉባዔው ለአስመራጭ ኮሚቴው አባልነት አስር (10) ዕጩዎችን አቅርቦ በሚያገኙት ድምፅ ቅደም ተከተል መሠረት አምስት(5) አባላትን ይመርጣል። የተቀሩትንም በተጠባባቂነት ይይዛል።

3.5 ጠቅላላ ጉባዔው የአስመራጭ ኮሚቴ አባሎችን በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መሠረት ይመርጣል።

3.6 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ውጤት ምርጫው በተከናወነበት ዕለት ይገለፃል።

3.7 የአስመራጭ ኮሚቴው የሥራ ዘመን ጠቅላላ ጉባዔው ከመጠራቱ ከስድስት ወር በፊት ጀምሮ የቦርድ አባላት ምርጫ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እስኪፀድቅ ድረስ ይሆናል።

## 4. የአስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛና የአባላቱ ስብጥር

4.1 የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት፦

ሀ) ባለአክሲዮን የሆኑ፣

ለ) በኮሚቴ አባልነት ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ፣

ሐ) የባንኩ ተቀጣሪ/ሠራተኛ ያልሆኑ፣

መ) ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ፣

ሠ) በኢትዮጵያ ወይም በየትኛውም የዓለም ክፍል ህዝብን በእምነት ማጉደል ወይም ከመጭበርበር ለመጠበቅ የወጣውን ህግ በመጣስ ወንጀለኛ ስለመባላቸው ማስረጃ ያልተገኘባቸው መሆን አለባቸው።

4.2 ከአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ዉስጥ ቢያንስ ሁለቱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸው።

4.3 የቦርድ አባላት የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም።

## 5. የዳሬክተሮች ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

5.1 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ከሚካሄድበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በፊት ለጠቅላላ ጉባዔው እንደ አጀንዳ እንዲቀርብ ያደርጋል።

5.2 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ምርጫ ያስፈፅማል።

5.3 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን አበል በጠቅላላ ጉባዔ ያስወስናል።

5.4 ለአስመራጭ ኮሚቴው ሥራ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ እና የሰው ሀይል ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል።

## 6. የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

6.1 የአስመራጭ ኮሚቴው በሚያከናውነው የመጀመሪያ ስብሰባ ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይመርጣል።

6.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የዕጩዎች ማቅረቢያና ምርጫ ማስፈፀሚያ የፀደቀ መመሪያ በተመለከተ በባንኩ የሚዘጋጅ ሥልጠና ይወስዳል።

6.3 ለቦርድ አባልነት የዕጩዎች ምልመላ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የቦርድ አባላት ምርጫ ያስፈፅማል።

6.4 ለቦርድ አባልነት የዕጩዎች ጥቆማና የምርጫ ሂደት ግልፅነትን፣ ፍትሃዊነትንና ተአማኒነትን መሠረት ያደረገና በሀገሪቱ ሕግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያና በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት የተካሄደ መሆኑን ያረጋግጣል።

## 7. የአስመራጭ ኮሚቴው ደንብና ሥርዓት

7.1 አስመራጭ ኮሚቴው ስብሰባዎች የሚያካሂዱበትን ቀን፣ ጊዜና ቦታ ይወስናል።

7.2 አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የአስመራጭ ኮሚቴው ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

7.3 ኮሚቴው ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖረዋል።

7.4 ኮሚቴው ውሳኔዎችን በድምፅ ብልጫ ያሳልፋል፣ ሆኖም የድጋፍና የተቃውሞ ድምፅ እኩል ከሆነ፣ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል።

7.5 የኮሚቴው ሰብሳቢ አስመራጭ ኮሚቴውን ይመራል፣ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ስብሰባ ይጠራል፣ ደብዳቤዎችን ይፃፋል፣ የኮሚቴው የስብሰባ ሂደቶችና ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ መስፈራቸውን ያረጋግጣል።

7.6 የኮሚቴው ፀሐፊ፣ ቃለ-ጉባዔዎችን ይይዛል፣ የኮሚቴውን ሠነዶች በጥንቃቄ ይጠብቃል፣ የኮሚቴውን የጽሕፈት ቤት ሥራ ይመራል።

7.7 ቃለ-ጉባዔዎቹ ተከታታይ ቁጥር ይኖራቸዋል፣ በስብሰባው በተገኙ አባላቱም ይፈረማሉ፣

7.8 ከአስመራጭ ኮሚቴው አባላት መካከል ሃምሳ በመቶ (50%) በታች የሚሆኑት በዚህ መመሪያ መሠረት የተመረጡበትን ጊዜ ሳይጨርሱ ቢለቁ ቀሪዎቹ የኮሚቴ አባላት ከተጠባባቂዎቹ መካከል ኮሚቴውን ለመመስረት ቀደም ሲል በተካሄደ ምርጫ ወቅት ባገኙት ድምፅ መሠረት የተጓደለውን ቦታ ይሞላል።

7.9 ቀሪዎቹ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከሃምሳ በመቶ (50%) በታች ከሆነ ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ሥራቸውን ያቆማሉ።

7.10 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 7.9 በተጠቀሰው መሠረት የአስመራጭ ኮሚቴው ሥራውን ካቆመ፣ ቦርዱ ጉዳዩን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል። በተጨማሪም በንግድ ሕግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና በባንኩ መመስረቻ ፅሁፍ መሠረት በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋል።

7.11 የአስመራጭ ኮሚቴው ኃላፊነቱን ግልፅ፣ ፍትሃዊ፣ ታአማኒ እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት እንዲሁም በባንኩ የዕጩዎች ማቅረቢያና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሠረት ሳያከናውን በመቅረቱ ምክንያት ምርጫው በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ የአስመራጭ ኮሚቴው ከአጠቃላይ የስራው ዋጋ ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይጣልበታል።

7.12 ለአስመራጭ ኮሚቴው አባላት ወርሃዊ አበል በጥቅል ብር 10,000 (አስር ሺ ብር) ይከፈላቸዋል።

## 8. ለዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን የማቅረብ ሂደት

8.1 አስመራጭ ኮሚቴው ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎችን የማቅረብ እንቅስቃሴ መጀመሩን ሰፊ ስርጭት ባላቸው የሕትመትና የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች በማሳወቅና እንደ አስፈላጊነቱ ደብዳቤ በመላክ ወይም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት ባለአክሲዮኖች ዕጩዎችን እንዲጠቁሙ ይጋብዛል።

8.2 ማስታወቂያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላት ማሟላት የሚገባቸውን አነስተኛ መስፈርትና ለዕጩ ማቅረቢያ የሚያገለግለውን ቅፅ ያካትታል።

8.3 አስመራጭ ኮሚቴው ለዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባልነት ጥቆማ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ይወስናል፣ ሆኖም ከሦስት ወራት ማነስ የለበትም።

8.4 የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት በዕጩነት አይቀርቡም።

8.5 አስመራጭ ኮሚቴው ሥራውን ለማከናወን ይችል ዘንድ ጊዜያዊ ቢሮ ከጊዜያዊ ሠራተኞች ጋር ይመደብለታል፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላት ስም የሚሰፍርበት መዝገብም ያዘጋጃል።

8.6 አስመራጭ ኮሚቴው፣ በዕጩ ማቅረቢያ ግዜ ገደብ ውስጥ ሁሉም ባለአክሲዮኖች ዕጩዎችን እንዲያቀርቡ ያተጋል።

8.7 የአስመራጭ ኮሚቴ ዕጩዎችን ባገኙት የዕጩነት ድምፅ መሠረት በቅደም ተከተል ይለያል፣ እንዲሁም በተገቢው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና ሌሎች ህጎች መሠረት የተቀመጠውን መመዘኛ እንደሚያሟሉ ያረጋግጣል።

8.8 አስመራጭ ኮሚቴው ቀጥሎ ያሉት ሁኔታዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት:-

ሀ) ከጠቅላላው የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ወስጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ቢያንስ ሰላሳ በመቶ (30%) የሚሆነውን በባለቤትነት የያዙና በጥቆማው የተሳተፉ እንደሆነ ለቦርድ አባልነት ዕጩ ሆነው ከሚቀርቡት መካከል አንድ ሦስተኛ (1/3ኛ) የሚሆኑትን ዕጩዎች የሚጠቁሙት እነዚሁ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ መሆናቸውን፣

ለ) ከጠቅላላው የተፈረመ ካፒታል ወስጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ከሰላሳ በመቶ (30%) በታች የሚሆነውን በባለቤትነት የያዙና በጥቆማው የተሳተፉ እንደሆነ ለቦርድ አባልነት ዕጩ ሆነው ከሚቀርቡት መካከል አንድ አራተኛ (1/4ኛ) የሚሆኑትን

ዕጩዎች የሚጠቁሙት እነዚሁ ተፅዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ መሆናቸውን፣

ሐ) እንደሁኔታው ቀሪዎቹ ሁለት ሦስተኛ (2/3ኛ) ወይም ሦስት አራተኛ (¾ኛ) ዕጩዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች መጠቆማቸውን፣

መ) በባንኩ ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች ከሌሉ ከላይ የተቀመጡት ንዑስ አንቀጾች ተፈፃሚነት የላቸውም።

8.9 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 8.8 የተገለፀውን ስብጥር ለማረጋገጥ፣ ኮሚቴው ከዕጩዎቹ መካከል የቦርድ አባላቱን ሁለት ሦስተኛ (2/3ኛ)ወይም ሦስት አራተኛ (¾ኛ) የሚሆኑትን በሁሉም ተሳታፊ ባለአክሲዮኖች ድምፅ በማስመረጥ እንደሁኔታው ቀሪዎቹን የቦርድ አባላት አንድ ሦስተኛ 1/3ኛ) ወይም አንድ አራተኛ(¼ኛ) እጩዎች ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች በተሰጡ ድምፆች ብቻ ያስመርጣል፣

8.10 በንዑስ አንቀፅ 8.8 የተጠቀሰውን ስብጥር መጠበቅ ካልተቻለ አስመራጭ ኮሚቴው ማስተካከያ ያደርጋል። ስብጥሩን ለማስተካከል ኮሚቴው በቅድሚያ የአንድ ሦስተኛ (1/3ኛ) ወይም የአንድ አራተኛ (1/4ኛ) ዳይሬክተሮችን ምርጫ በማከናወን ቀጥሎ እንደሁኔታው የሁለት ሦስተኛ (2/3ኛ) ወይም የሦስት አራተኛ (3/4ኛ) ዳይሬክተሮችን ምርጫ ያካሂዳል፣

8.11 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚቀርቡት ዕጩዎች ቁጥር ለቦርድ አባልነት ከሚመረጡት ቁጥር እጥፍ ይሆናል። ለመመረጥ ፈቃደኛ ባልሆኑ ዕጩዎች በታ ለመተካት እንዲቻል ኮሚቴው ከመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ በጥቆማው ሂደት ባገኙት ድምፅና ስብጥሩን በጠበቀ ሁኔታ የአምስት (5) አባላትን ዝርዝር በተጠባባቂነት ይይዛል፣

8.12 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩዎች የሚመረጡት በባለአክሲዮኖች በሚያገኙት የድምፅ ብዛት መሠረት ይሆናል። ዕጩ ዳይሬክተሮች እኩል ድምፅ ካገኙ አስመራጭ ኮሚቴው የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና ሌሎች ደጋፊ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ብልጫ ያላቸውን ዕጩዎች ይለያል፣

8.13 የአስመራጭ ኮሚቴው እጩዎች ባገኙት የእጩነት ድምፅ መሠረት ጨምቆ ያዘጋጀውን የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ስም ዝርዝር ምርጫውን ለማካሄድ ጉባዔ ከመጠራቱ አንድ ወር አስቀድሞ፣

ሀ) ሁሉም ጎብኝዎችና ደንበኞች ማየት እንዲችሉ በባንኩ ዋና መ/ቤት እና በሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች ግልፅ በሆነ ቦታ ይለጥፋል፣

ለ) ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ያሳትማል፣

ሐ) በባንኩ ድረ ገፅ ላይ ያወጣል፣

8.14 አስመራጭ ኮሚቴው ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚወዳዳሩትን ዕጩዎች ዝርዝር ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች በማካተት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡

ሀ) ስምና ዕድሜ፣

ለ) በጥቆማ የተሰጠው የድምፅ ብዛት፣

ሐ) የትምህርት ደረጃ፣

መ) የሥራ ልምድ፣

ሠ) በባንኩ ውስጥ የቦርድ አባል ሆኖ በማገልገል ላይ ያለ ከሆነ፣ መሆኑንና በሌሎች በታዎችም በኃላፊነት እየሰራ ከሆነ ይህንኑ፡፡

8.15 በዚህ መመሪያ መሠረት በሚካሄድ የዳሬክተሮች ቦርድ አባልነት ምርጫ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዕጩነት ከተጠቆመ አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩውን በቦርድ ውስጥ የሚወክለው ሰው በጥቆማው ሂደት እንዲታወቅ ማድረግና ለቦርድ አባልነት መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

8.16 አስመራጭ ኮሚቴው ለዳይሬክተርነት የሚያቀርባቸው ዕጩዎች ስብጥርን በሚመለከት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸው ሕጎች ያሰፈሯቸውን መስፈርቶች የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

8.17 የቀረቡት የቦርድ አባላት ዕጩዎች ቁጥር በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው በታች ከሆነ ወይም ዕጩዎቹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን መመዘኛ ካላሟሉ አስመራጭ ኮሚቴው እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የብሔራዊ ባንክን መመሪያ የሚያሟሉ ዕጩዎች እንዲገቡ የሚቻለውን ያደርጋል፡፡ በቂ ዕጩዎችን ማግኘት ካልተቻለ ግን ችግሩን ለጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ ጉባዔው ከመካከሉ እጩዎች እንዲጠቁምና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

## 9. የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ ሂደት

9.1 አስመራጭ ኮሚቴው ከዳይሬክተሮች ቦርድ ፣ ከማኅበሩ ፀሐፊ እና ከድምፅ ቆጣሪዎች ጋር በመተባበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ያከናውናል።

9.2 ለዕጩነት የሚቀርቡት የቦርድ አባላት ቁጥር 24 ይሆናል።

9.3 አስመራጭ ኮሚቴው የዕጩ ቦርድ አባላትን ዝርዝር ከነታሪካቸው ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል።

9.4 አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩ የቦርድ አባላትን እራሳቸውን ለጠቅላላ ጉባዔው እንዲያስተዋውቁ እና በቦርድ አባልነት ለመሥራት ፈቃደኛነታቸውን እንዲገልፁ ዕድል ይሰጣቸዋል።በዕለቱ በአስገዳጅ ምክንያት ለጠቅላላ ጉባዔ እራሳቸውን ማስተዋወቅ ባይችሉ አስመራጭ ኮሚቴው የቀረበውን ምክንያት አሳማኝነት ከግምት በማስገባት በምርጫው ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል።

9.5 አስመራጭ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው የባንኩ አካላት ጋር በመተባበር፣ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሳጥኖችን ያዘጋጃል።

9.6 የድምፅ መስጫው ወረቀት የሚከተሉትን ይይዛል፡-

ሀ) የባለአክሲዮኑን ስም፣

ለ) የባለአክሲዮኑን የተፈረመ አክሲዮን ብዛት፣

ሐ) ለጉባዔው ሲባል የተሰጠ መለያ ቁጥር፣

መ) የባንኩ ስምና አርማ፣

ሠ) የባንኩ ማህተም፣

ረ) ባለአክሲዮኑ የሚመርጣቸውን ዕጩዎች ስም የሚጽፍበት ባዶ ቦታ።

9.7 የምርጫ ወረቀት ዕደላ በጉባዔው ለመሳተፍ የመጡ ባለአክሲዮኖች ምዝገባና ፊርማ በሚካሄድበት ወቅት ይከናወናል፣ የምርጫው ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ አስመራጭ ኮሚቴው የምርጫውን ሂደት በቅርብ ይከታተላል።

9.8 ማንኛውም ዕጩ በቦርድ አባልነት ለመመረጥ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከተሰረዘ ከተጠባባቂዎቹ መካከል ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው እንዲተካ ተደርጎ ምርጫው ይካሄዳል።

## 10. <u>የምርጫ አፈፃፀም ሥርዓት</u>

10.1 ባለአክሲዮኖች የሚመርጧቸውን ዕጩዎች ሙሉ ስም በምርጫ ወረቀቶቹ ላይ በመጻፍ ወረቀቶቹን በተዘጋጁት ሳጥኖች ውስጥ ይከታሉ።

10.2 በአካል በመገኘትና በውክልና የሚሰጥ ድምፅ በባንኩ የመመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት ይከናወናል። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን የራሱን ጨምሮ ከተፈረመው የባንኩ ካፒታል ከአስር በመቶ (10%) በላይ አክሲዮን ያላቸውን ሊወክል አይችልም።

10.3 ድምፅ አሰጣጡ ከተከናወነ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው ከዳሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ከድምፅ ቆጣሪዎች፣ የማህበሩ ፀሐፊ እና ድጋፍ ሰጪዎች ጋር በመሆን ድምፅ ቆጠራውን ያካሂዳል።

10.4 አስመራጭ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጡትን ድምፆችና ውድቅ የተደረጉ ካርዶችን ይመዘግባል፣ ውድቅ በተደረገ የድምፅ መስጫ ካርድ ላይ ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት ያሰፍራል፣ ይኸው በኮሚቴው ተረጋግጦ ይፈረምበታል።

10.5 የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ውድቅ ይደረጋል፡-

ሀ) የባለአክሲዮኑን ስም ካልያዘ፣

ለ) የባለአክሲዮኑን የተፈረመ አክሲዮን ብዛት ካላሳየ፣

ሐ) የባንኩን ስምና ዓርማ ካልያዘ፣

መ) የዕጩ ተወዳዳሪው ስም ካልተፃፈበት፣

ሠ) በመራጩ ያልተፈረመ ከሆነ፣

ረ) ስርዝ ድልዝ ካለበት፣

ሰ) የባለአክሲዮኑን የመለያ ቁጥር ካልያዘ፣

10.6 የድምፅ ቆጠራው ከተጠናቀቀ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው የምርጫውና የቆጠራው ሂደት እንዲሁም የምርጫው ውጤት ትክክል መሆናቸውን በተያዘው ቃለ-ጉባዔና ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ይወጣል።

10.7 የተቆጠረው ድምፅ ታሽጎ ለብቻው ይቀመጣል።

10.8 የድምፅ ቆጠራው ውጤት በዕለቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ይገለፃል።

## 11. <u>ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የማይሆንበት ሁኔታ</u>

11.1 ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የማይሆነው በሥራ ላይ ካሉት የቦርድ አባላት ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ የሚሆኑት፡-

ሀ) የሥራ ዘመናቸው ከማለቁ በፊት በጠቅላላ ጉባዔው ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲነሱ ከተደረገ፣

ለ) በገዛ ፈቃዳቸው ከቦርድ አባልነት ከለቀቁ፣

ሐ) በተለያዩ ምክንያቶች በቦርድ አባልነት መቀጠል ካልቻሉ ወይም

መ) በአስመራጭ ኮሚቴው የቀረቡት ዕጩዎች በጠቅላላ ጉባዔው ከተሰጠው ድምፅ ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ በሚሆነው ተቀባይነት ሲያጡ።

11.2 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 11.1 የተመለከቱት ሲያጋጥሙ የቦርድ አባላት ምርጫ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት ይከናወናል።

11.3 ከቦርድ አባላት መካከል ከሃምሳ በመቶ (50%) በታች የሆኑት የሥራ ጊዜያቸው ከማለቁ በፊት ቢለቁ የተጓደሉትን ዳይሬክተሮች ለሟሟላት የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይካሄዳል።

## 12. መመሪያ ስለማዘጋጀት

አስመራጭ ኮሚቴው ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 13. ሌሎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሕጎች

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ የሀገሪቱ ሕጎች እና የባንኩ መመስረቻ ፅሁፍ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## 14. ይህ መመሪያ በጥብቅ ስለመፈፀሙ

የአስመራጭ ኮሚቴ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የዕጩዎች ማቅረቢያና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ በጥብቅ በሥራ ላይ ያውላል።

## 15. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሠረት ማሻሻያው የብሔራዊ ባንክን መመሪያ እስካልጣሰ ድረስ ሊሻሻል ይችላል።

## 16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በጠቅላላ ጉባዔው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ፀሐይ ባንክ አክሲዮን ማህበር**